# በመዝጊያ ላይ የተሰጡ ቃላት

ፕሬዘደንት ቶማስ ኤስ ሞንሰን

ውድ ወንድሞቼ እና እህቶቼ፣ ከሁሉም በላይ ያነሳሳው ጉባኤ መጨረሻ ላይ ደርሰናል። ያነጋገሩንን ምክሮች እና ምስክሮች ከሰማን በኋላ፣ እንደተባረክን እና በኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል መሰረት ለመኖር ውሳኔ አድርገናል። በዚህ መሆን ለእኛ መልካም ነበር። ላነጋገሩንና ጸሎት ላቀረቡልንም ምስጋናችንን እናቀርባለን

ሙዚቃው አስደናቂ ነበር። በትምህርት እና ቃል ኪዳን ውስጥ ያለውን ቅዱስ መጻህፍት እንዳስታውስ ያደረገኛል፤ "በልብ መዝሙር ነብሴ ትደሰታለች፣ አዎ የጻድቅን መዝሙር ለእኔ ጽሎት ነው፣ በርከት በራሳችው ላይ በማድረግ ይመለስላችዋል።"

<u>በዚህ ጉባኤ የሰማናቸው መልእክቶች በግንቦት በሚታተሙት </u>Ensign እና Liahona ገጼቶች ውስጥ እንደሚገኙ አስታውሱ። መልእክቶችን እንድታጠኑ ፣ ያስተማሩትን እንድታሰላስሉ፣ እና በህይወታችሁም እነዚህን እንድትጠቀሙባቸው አበረታታችኋለሁ።

በዚህ ጉባኤ ከሀላፊነታቸው የተለቀቁትን ከእኔ ጋር ለአገልግሎታቸው ምስጋና እንደምትሰጡ አውቃለሁ። በደንብ አገልግለዋል እና ለጌታ ስራም ታላቅ ድጋፍ ሰጥተዋል። ስራውን ለማክከናወን የነበራቸው ፍላጎት ሙሉ ነበር። በጣም እናመሰግናቸዋለን።

እጆቻችንን በማንሳትም በዚህ ጉባኤ ለአዲስ ሀላፊነት የተጠሩትን ወንድሞችና እህቶች ደግፈናል። በመምህር ስራም ላይ ከእነርሱ ጋር ለመስራት እንደምንጠብቅ እንዲያውቁ እንፈልጋለን።

ወንድሞቼ እና እህቶቼ፣ ዛሬ የአካባቢያችንን አለም ስንመለከት፣ የሚያሳስቡን ችግሮች እያጋጠሙን ነን። አለም ከሰላም እና ደህንነት ተርቆ እየሄደ ነው።

ማንኛውንም ተቀባይ መሆን፣ ስነምግባር የሌለ መሆን፣ ወስባዊ ነገሮች፣ እና ውሸተኛነት እና ሌሎች ክፎዎች በኀጥያት እንዲሰቃዩ እና እድልን እንዲያጡ፣ በረከቶችን እንዲያጠፉና የሚያልሙትንም እንዲሰበርባቸው አድርገዋል።

ለሁላችንም ያለኝ ምክር ቢኖር ወደ ጌታ እንድንመለከት ነው። የእርሱ ብርሀን በጭጋግ፣ በጭለማ፣ ወይም በታላቅ ንፋስ የሚጠፉትን ለማዳን የሚችል ነው። እርሱም ወዲያው የሚታወቅን እና የማይወድቅን ብርሀኑን ይልካል።

"እግዚአብሔር ዓለቴ፥ አምባዬ፥ መድኃኒቴ፥ አምላኬ፥ በእርሱም የምተማመንበት ረዳቴ፥ መታመኛዬና የደኅንነቴ ቀንድ መጠጊያዬም ነው። ...እግዚአብሔርን እጠራለሁ፥ ከጠላቶቼም እድናለሁ" የሚሉትን የመዝሙርን ቃላት እወዳለሁ።

ወንድሞች እና እህቶች ጌታ ይወደናል፤ እና እርሱን ስንጠራም ይባርከባል።

ዳግሞ ለተመለሰው ለኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል እና በህይወቶቻችን ለሚያመጣው ጥሩ ነገሮች ምን አይነት ምስጋና ነው ያለን። ለሁላችንም ጌታ በረከቶቹን አፍስሶልናል። ይህ ስራ እውነት እንደሆነ፤ አዳኛችን ህያው እንደሆነ፤ እና በዚህች ምድርም ቤተክርስትያኑን እንደሚመራ እመሰክራለሁ። ለዚህ ጉባኤ መጨረሻ ጊዜ ስንመጣም፤ ልቤ በስሜታ ተሞልቷል፤ ስሜታዎቼም ተነሳስተዋል። ለእናንተ ያለኝን ፍቅር እና ምስጋና ለመግለፅ እፈልጋለሁ። ለእኔና ለአጠቃላይ ባለስልጣናት በሙሉ ለምትጸልዩት ምስጋና አቀርባለሁ። ጌታ ጸሎታችሁን ይሰማል እና ይባርከናል እና በዚህች ምድር ላይ ያለችውን መንግስቱን ጉዳያት ይመራል። ለዚህም ዝልቅ ምስጋና አለን።

ከዚህ ጉባኤ ስንሄድ፤ በእያንዳንዳችሁ ላይ የሰማይ በረከትን እጠራላችኋለሁ። በአለም ውስጥ ወዳሉት ወደቤቶቻችሁ ስትመለሱ፤ የሰማይ አባታችን እናንተን እና ቤተሰቦቻችሁን እንዲባርካችሁ እጸልያለሁ። የዚህ ጉባኤን መልእክት እና መንፈስ በምታደርጉት ሁሉ፤ በቤቶቻችሁ፤ በስብሰባዎቻችሁ፤ እና በምታደርጉት ሁሉ ተጠቀሙበት።

እወዳችኋለሁ። እጸልይላችኋለሁ። እግዚአብሔር ይባርካችሁ። የእርሱ ሰላይ ከእናንተ ጋር አሁንም ሁልጊዜም እንዲገኝ የምጸልየው በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ነው፤ አሜን።